# መክሊት ማይክሮፋይናንስ ኢንስቲትዩሽን አ.ማ.

## መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ንግድ ህግ አንቀፅ 366(1)፣ 367(1 እና 2)፣ አንቀፅ 372 መሰረት መክሊት ማይክሮፋይናንስ ኢንስቲትዩሽን አ/ማ የባለአክሲዮኖች 16ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ታህሳስ 05 ቀን 2017 ዓ.ም ከጠዋቱ 2:30 ሰዓት ጀምሮ በአዲስ አበባ ሆቴል በሚገኘው ኢሊሊ ሆቴል ግሪን አዳራሽ ያካሂዳል። በመሆኑም የተከበራችሁ የአክሲዮን ማህበሩ ባለአክሲዮኖች በዕለቱ በጉባኤው ላይ እንድትገኙልን የማህበሩ ዳይሬክተሮች ቦርድ ጥሪውን ያስተላልፋል።

1. ማህበሩን የሚመለከቱ ዋና ዋና መረጃዎች

   1.1. የአክሲዮን ማህበሩ ዋና መስሪያ ቤት አድራሻ

   - አዲስ አበባ፣ ለሚኩራ ክ/ከተማ፣ ወረዳ 13 ልዩ ቦታ ሲ.ኤም.ሲ የተባበሩት ፀሀይ ሪልስቴት ፊት ለፊት አዲስ አፍሪካ አለም አቀፍ ኮንቬንሽንና ኤግዝቢሽን ማዕከል አንደኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 106 የቤት ቁጥር አዲስ።
   - ስልክ ቁጥር 011-3-48-41-52 ፖ.ሳ. ቁጥር 27634/1000
   - ድሕረ-ገጽ www.meklitmicrofinance.com

   1.2. የማህበሩ የምዝገባ ቁጥር፡ BLAA/3/0024436/2013

   1.3. የማህበሩ የተፈረመ ዋና ገንዘብ (ካፒታል) ብር 154,142,000.00

   1.4. የማህበሩ የተከፈለ ዋና ገንዘብ (ካፒታል) ብር 154,142,000.00

2. የመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች

   1. የጉባኤውን ፀኃፊ መሰየም፣
   2. ድምጽ ቆጣሪዎችን መሰየም፣
   3. ምልአተ ጉባኤ መሟላቱን ማረጋገጥ፣
   4. አጀንዳ ማፅደቅ፣
   5. ለነባርና አዳዲስ ባለአክሲዮኖች የተሸጡ አክሲዮኖችንና የአክሲዮን ዝውውሮችን ማፅደቅ፣
   6. የ2016 ሂሳብ ዓመት የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርት ማዳመጥና ማፅደቅ፣
   7. የ2016 ሂሳብ ዓመት የውጭ ኦዲተሮችን ሪፖርት ማዳመጥና ማፅደቅ፣
   8. ለዳይሬክተሮች ቦርድ የሚከፈል ዓመታዊ ክፍያ ላይ ተወያይቶ መወሰን፣
   9. የ2016 ሂሳብ ዓመት ትርፍ ክፍፍል ላይ ተወያይቶ ውሳኔ ማሳለፍ፣
   10. የተቋሙ ካፒታል መጠባበቂያ (Capital Reserve) በተያዘ ገንዘብ ላይ ተወያይቶ ውሳኔ ማሳለፍ፣
   11. የውጪ ኦዲተር ምርጫ ማካሄድና ማጽደቅ፣

12. የጉባኤውን ቃለ ጉባኤ ማጽደቅ፣

3. ማሳሰቢያዎች

3.1. ማንኛውም ባለአክሲዮን ከላይ በተጠቀሰው ዕለት እና ቦታ ተገኝተው እንዲሳተፉ ተቋሙ ጥሪ ያቀረበ ሲሆን በጉባኤው ላይ መገኘት የማይችሉ ባለአክሲዮኖች በንግድ ሕጉ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 አንቀጽ 377 መሠረት ጉባኤው ሊካሄድ 3 ቀን ሲቀረው ከላይ በተጠቀሰው የማህበሩ ዋና መስሪያ ቤት አድራሻ በአካል ቀርበው የውክልና ፎርም በመሙላት ተወካይ እንዲሰይሙ እናሳስባለን፡፡

3.2. ሁሉም ባለአክሲዮኖች ማንነታቸውን የሚገልጽ የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ፣ፖስፖርት ወይም የመንጃ ፍቃድ ይዘው እንዲቀርቡ በአክብሮት ይጠይቃል፡፡

መክሊት ማይክሮፋይናንስ ኢንስቲትዩሽን አ.ማ

የዳይሬክተሮች ቦርድ